# ምን ነካው አማራ

ዘመን ተለውጦ ፣ ያልሆነ እየሆነ
የምንሰማው ሁሉ ፣ ሆነ ያልታመነ
ኮሽ ሲል የሚሮጥ ፣ እየተበተነ
ፈሪም እንደ ጀግና ፣ ልቡ ደነደነ
ሲሸሽ የምናውቀው ፣ አዳኙን አደነ
አለቱ ኮሰሰ ፣ ቅሉ እንኳን ጀገነ ።

ሁሉም በአማራው ላይ ፣ ተነስተው ሲዘምቱ
ከግራም ከቀኝም ፣ ሲንጋጋ መዓቱ
ባዕድ እንኳን ቢሆን ፣ በሰው ልጅነቱ
ቻል አለው ወንድሙ ፣ ፈሰሰ ሃሞቱ
አልቆረቆር አለው ፣ አልተሰማው ሞቱ
መከታ እንዳይሆነው ፣ ዛለ ወይ ጉልበቱ?
ቀድሞ የምናውቀው ፣ የብርቱዎች ብርቱ
ምን ነካው አማራ ፣ ዝምታ ማብዛቱ ።

አማራው ተከቦ ፣ ዙሪያውን ባራጁ
መመከት አቅቶት ፣ አባትም ለልጁ
ልጁን እናቱ ፊት ፣ ሲደፉት ከደጁ
በገጀራ ታርደው ፣ በእሳት ሲፈጁ
ለአማራው ስቃይ ፣ ሆነው ወይ ወዳጁ
እግዜሩም ዝም አለ ፣ የእውነት ፈራጁ ።

የወገኑ ማለቅ ፣ መርገፍ እንደሾላ
ትንሹም ትልቁም ፣ በቀን ጅብ ሲበላ
በጭካኔ ሲያርዱት ፣ አንገቱ ሲቀላ
ባቀናት አገር ላይ ፣ ሰርቶ እንኳ እንዳይበላ
ፍትህ ባገር ጠፍቶ ፣ አላግባብ ሲጉላላ
አማራው ምን ነካው ፣ ጽዋው የማይሞላ?
ሰምቶም እንዳልሰማ ፣ አይቶም እንዳላየ
… ለምን ይላል ችላ ።

እኔን ግራ ገባኝ ፣ የአማራው ዝምታ
ለትንሽ ትልቁ ፣ በቀላል ተፈታ
እንኳን ጦር ሊያነሳ ፣ ሊሆነው መከታ
ዱላው ተሰወረ ፣ ሆነ የውሃ ሽታ
ዋይታው መሰለው ወይ ፣ ሳቅና ደስታ
እንቆቅልሽ ሆነ ፣ አለኝ አልፈታ
ምን ነካው አማራው ፣ አበዛ መኝታ ።

ታዛቢው

June 6, 2018